# የብሄረሰቦች ቀን በዓል ፋይዳዎች

*ዮናስ ገረመው (yonasgeremew46@yahoo.com)*

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዝያ 21/1998 ዓ.ም በሶስተኛው የፓርላማ ዘመን አንደኛ ዓመት የሥራ ዘመን ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባው የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ዋስትና የሆነው የኢፌዴሪ ህገመንግሥት የፀደቀበትን ህዳር 29 ቀን የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን ሆኖ በየዓመቱ በተለያዩ ዝግጅቶች እንዲከበር በወሰነው መሠረት የ17 ዓመታትን ዕድሜ ያስቆጠረው የህገመንግሥታችን ዕለተ ቀን በ6ኛው የብሔረሰቦች ቀን በተረኛው ክልል ትግራይ መቀሌ ከተማ የሚከበርበት ዋዜማ ላይ እንገኛለን፡፡

ከዚህ ቀደም የነበሩት አምስቱም የብሔረሰቦች ቀን ክብረ በዓላት በተለያዩ መሪ ቃሎች የተከበሩ ሲሆን አምስተኛውንና አዲስ አበባ ላይ የተከበረውን በዓል መሪ ቃል ብናስታውስ "የብሔረሰቦች ቀን በዓል የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘን የአገራችንን ህዳሴ ወደማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እናደርሳለን" የሚል ነበር፡፡ የዘንድሮው ክብረ በዓል ደግሞ "ህገ መንግሥታችን ለብዙህነታችን፣ ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ቃል የሚከበር እንደሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው በጋራ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል፡፡

የዛሬው መጣጥፌ የትኩረት አቅጣጫም የበዓሉ መከበርን ፋይዳና በህገመንግሥቱ ዋስትና ስላገኘው የፌዴራላዊ ሥርዓት ተግዳሮቶች ወይም የተለዩ ምልከታዎች መቃኘት ነው፡፡ የብሔረሰቦች ቀንንና ፌዴራላዊ ሥርዓቱን በጥምረት ለመቃኘት መነሻ የሆነኝ ምክንያት አንድም ህገመንግሥቱ በፀደቀበት ወርሃ ህዳር ላይ በመገኘታችን ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጉዳይና ፌዴራላዊ ሥርዓቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች በመሆናቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አንዱ በአንዱ ተደጋግፎ የቆመና የማይነጣጠሉ አጀንዳዎች በመሆናቸው ነው፡፡

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር እንደመሆኗ ዜጎች ተፈቃቅደውና ተከባብረው እንዲኖሩ የፌዴራል ሥርዓቱ አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የተለያዩ ቋንቋዎች ባህሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስተጋብሮች ባሉባት ኢትዮጵያ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ መደረጉም ዕጣ ፋንታቸውን እንዲወስኑ አስችሏቸዋል፡፡ የፌዴራል ሥርዓት ለሁሉም ክልሎች የተወሰነ ስልጣን ስለሚሰጥ በማዕከላዊ መንግሥትና ክልሎች መካከል ሊኖር የሚችለውን ውጥረት ለማርገብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡የፌዴራሊዝም ስርአቱ አስተዋጽኦ በዚህ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በፌዴራል አወቃቀር አማካኝነት የመልካም አስተዳደር ወደታችኛው የመንግሥት መዋቅር እንዲወርድ መደረጉም የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው እንዲጠናከር ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ቀደም ሲል ስልጣን ላይ በነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት ስልጣን በማዕከል እንዲከማች መደረጉ የህዝቡን ተሣትፎ የገደበ በመሆኑ ኢትዮጵያን ለመሰሉ ትልቅ እና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች አገር የፌዴራል አደረጃጀት አስፈላጊ ነው ብሎ መደምደም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታችንን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ተጠቃሚነታችንንም ያረጋገጠ በመሆኑ በብዝሀነታችን አንድ ሆነን በእኩልነት እንኖራለን ስንል ቃልኪዳን ያሠርንበት ዕለት ነው ህዳር 29፡፡ ህዳር 29 ባስገኘልን ህገመንግሥታችን መሠረት የአገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የስልጣን ባለቤት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከፖለቲካ ጥቅሞቻቸው በተጨማሪ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስክ ተከታታይነት ያለው እድገት በማስመዝገብ የዕድገቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በመሆን የተሻሻለ ህይወት መምራት ከመጀመራችንም ባሻገር የውስጥ ሰላማችን አስተማማኝ ደረጃ ላይ በመድረሡም የህዳሴ ጉዞችንን በተሣካ ሁኔታ በማስቀጠል ላይ እንድንገኝ አስችሎናል፡፡

ፌዴራላዊ ሥርዓቱን በተመለከተ ቅሬታ አለን የሚሉ ወገኖች እንደሚያነሡት በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተና ጐሣና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ብቻ መሆን አልነበረበትም ሲሉ የህዝቦችን ታሪካዊ ትሥሥር ቋንቋ ባህልና ታሪካዊ ግንኙነቶች እንዲሁም የሃገሪቱን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ መሠረት ያረገ ሊሆን ይገባል የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በተዳጋጋሚ ያነሣሉ፡፡ ሁሉም ግን ሃገራችን ባለችበት ተጨባጭ ሁኔታ በአንድነት ፌዴራላዊ ሥርዓት ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ስለመሆኑ ያለመጠራጠር ይገልፃሉ፡፡ ይህ ደግሞ የፌዴራላዊ ሥርዓቱ በተዘረጋበት የመጀመሪያ ዓመታት ላይ በአንዳንድ ወገኖች

ዘንድ ይንጸባረቅ የነበረው አሉታዊና ጭፍን አመለካከት በሂደት እየጠራ የመጣ አቋም መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የፌዴራላዊ ሥርዓቱን አስፈላጊነትና ዳራ፤ ዋነኛና ተጨባጭ ዓላማዎች፤ ፋይዳውን፤ አወቃቀሩንና ከነዚህም ጋር ተያይዞ እየተስተዋሉ ያሉ አፍራሽ አመለካከቶችን በተመለከተ በተለያዩ አጋጣሚዎች ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠይቀው ምላሽና አስተያዬት ሲሠጡ እንደነበር አንዘነጋም፡፡

ፌዴራሊስት ዴሞክራሲ የሚባለው ሥርዓት ብዙሀነታችንን ለማስተናገድ ተመራጭ ስለመሆኑና ተመራጭነቱ ግን ከሃገር ሃገር እንደሚለያይ አብነቶችን በማንሣት የሚሞግቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዋቢ ያቸውን ከጀርመን ይጀምራሉ፡፡ በጀርመን የብሔር ልዩነት ከሞላ ጐደል አለመኖሩንና ልዩነቱ ከባቢያዊ መሆኑን በማስመር፡፡ ስለሆነም በጀርመን የሚኖረው ፌዴራላዊ ሥርዓት መሠረቱ ብሔርና ቋንቋ ሊሆን እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያን ሁኔታ ከዚህ አንፃር ስናይ ሃገሪቱን ለረጅም ጊዜ ሲያምስ የነበረውና ትልቁ አጀንዳ የብሔሮችና ብሔረሰቦች ጭቆና ነው፡፡ ስለሆነም ፌዴራላዊ ሥርዓቱ መቃኘት የሚገባውና መመለስ የሚገባው ጥያቄ ትልቅ ፈተና ለነበረው የብሔር ጥያቄ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በብቃት ማስተናገድ ማ ለት ደግሞ  በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምና በፍላጐት ላይ የተመሠረተ አንድነት መፍጠር ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸውንና የፌዴራሊዝም ሥርዓቱን በተመለከተ የሚነሱ ተቃራኒ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች ኢትዮጵያ እንደዩጎዝላቪያ ለብተና  ትዳረጋለች ብለው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲለፉና ሲያስለፍፉ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ግን ለብሔር ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሰጠው የፌዴራል ሥርዓቱ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ስጋት ሳይሆን ቀርቶ አንድነታችንን ጠብቀንና ሠላማችንን አስከብረን በጋራ እንድንለማ ለማድረግ ከምንጊዜውም በበለጠ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረልን የእስካሁኑ ጉዞአችንና ስኬታችን ግልጽ ማሳያ ነው፡፡

“ህገ መንግሥታችን ለብዝሀነታችን፣ ለአንድነታችንና ለሀዳሴያችን” በሚል መሪ ቃል የዘንድሮው የብሔረሰቦች ቀን የሚከበር እንደመሆኑ ስለ ብዙህነትና አንድነት በብዙህነትና አንድነት ስለሚገኝ ህዳሴ የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሳት ግድ ይላልና ወደኋላ እመለሳለሁ፡፡ በቅድሚያ ስለብሔረሠቦች ቀን በዓል ፋይዳ የተወሰኑ ነጥቦችን ላንሳ፡-

የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በአንድ መልኩ የኢትዮጵያ ዝቦችን ብዝሀነት አጉልቶ ለማሳየት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዝሀነቱን ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት እንደተገነባና ብዝሀነታችን የልዩነታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ እንደሆነ ለማስመስከር የሚያገለግል መድረክ በመሆኑ ትልቅ ትርጉምና ፋይዳ የሚሰጠው ነው፡፡ ለዚህም ነው በሃዋሳ ከተማ የተከበረው 2ኛው የብሔረሰቦች ቀን “ልዩነታችን ውበታችን፣ ውበታችን አንድነታችንና ጥንካሬያችን” ነው በሚል መሪ ቃል የተዘከረው፡፡ ወደ ሌሎች ዝርዝር የበዓሉ ፋይዳዎች ሣመራ “ ህገመንግሥታዊ ቃልኪዳን የአብሮነታችን መገለጫ ነው” በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ከተማ ከተከበረውና ከ1ኛው የብሔረሰቦች ቀን በዓል ጋር የተያያዘውን ህገመንግሥታዊ ፋይዳ መጀመሪያ ማንሣት ወደድኩ፡፡

የብሔረሰቦች ቀን በዓልን ማክበር ማለት ህገመንግሥቱ የፀደቀበትን ቀን መዘከር ማለት ነው፡፡ ህገመንግስቱን መዘከር ማለት ደግሞ ህገመንሥቱ ያስገኘልንን ጥቅሞችና ድሎች የበለጠ በመንከባከብ የተመዘገቡትንም የልማትና የመልካም አስተዳደር ውጤቶች በማስፋፋት ያለንን የእርስ በርስ መተጋገዝ በማጠናከር የበለጠ ቃል የምንገባበት በዓል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ህዝቦች በዴሞክራሲና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት፣ ለአገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም በወንድማማችነትና በመቻቻል አብሮ የመኖር ባህላቸውን የሚያንፀባርቁበት የነፃነትና የድላቸው ቀን በመሆኑ በታሪካዊነቱ የተለየ ቦታ ይሰጠዋል፣ ህዳር 29፡፡

የአገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በአገራችን እስካሁን ሲከናወኑ የቆዩት የልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተግባራት ዋነኛ ተሣታፊዎችና ተጠቃሚዎች እንደሆኑ የታመነ ነው፡፡ “ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንን በማጠናከር ልማታችንን

እናፋጥናለን” በሚል መሪ ቃል በኦሮሚያ ክልል የተከበረውን 3ኛውን የብሔረሰቦች ቀን ያስታውሷል፡፡ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በትግላቸው የመሠረቱት ፌዴራላዊ ስርዓት የህዝቦችን ሃብትና አቅም በመጠቀም ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን ለማምጣት የሚያስችል በመሆኑ ሁሉም የአገራችን ክልሎች በፈጣን ልማት ውስጥ እንዲገቡ አስችሏልና፡፡

ለዘመናት ተንሠራፍቶ የቆየውን ድህነትና ኋላ ቀርነት ለመደምሰስ የተደረገው ተጋድሎ ከዓመት ዓመት ለውጥ እያስመዘገበ መሆኑ አገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት አረንቋ እንደምትወጣ የአገሪቱ ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ መላ የዓለም ህዝቦች የሚመሰክሩበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በዚህ የተነሣም አገራችን በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቷ እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የብሔረሰቦች ቀን በዓል ደግሞ የአገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚያደርጉትን ሥርነቀል የልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅስቃሴ ለዓለም የሚያሣዩበትና ቃልኪዳናቸውን የሚያድሱበት በመሆኑ ፋይዳውን የበለጠ ጉልህ ያደርገዋል፡፡

“የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘን የአገራችንን ህዳሴ ወደማይቀለበስበት ደረጃ እናድርስ" በሚል መሪ ቃል ከተከበረው 5ኛው የብሔረሰቦች ቀን አንፃር የበዓሉን ፋይዳ ስንመዝነው ደግሞ ከሺህ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ህዝቦች በወቅቱ የሰለጠኑ ተብለው ከሚፈረጁት ህዝቦች መካከል የሚቆጠር ስልጣኔ የገነቡ ህዝቦች መሆናቸውን በማስታወስ አሁን ካለንበት አስከፊ ድህነት ወጥተን በፊት ወደ ነበርንበት የስልጣኔ እርከን በመመለስ ከሠለጠኑት ህዝቦች ጋር የምንሰለፍበትን ጉዞ መጀመራችንን የምናወሰባት ሲሆን በሌላ መልኩ ያለፈውን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱ ሥልጣኔ የሚገነባው በአዲስ መሠረት ላይ መሆኑን በመገንዘብ ካለፈው የኢትየጵያ ሥልጣኔ በተለየ ሁኔታ ሁሉም ህዝቦች እምነታቸውን ጠብቀው፣ባህልና ቋንቋቸውን አክብረው፤ ልዩነታቸውን አቻችለው በመፈቃቀድ በጋራ የሚኖሩበትና የሚሠሩበት፣ ሠርተውም እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አዲስ አቅጣጫ በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩንና ጅምሩም ብዙ ርቀት እንዲሄድ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቃልኪዳናቸውን የሚያድሡበትና ልምድ የሚለዋወጡበት በዓል ነው ህዳር 29፡፡

በአጠቃላይ በየአመቱ ህዳር 29 በምናከብረው የብሔረሰቦች በዓል፦ ብሔር ብሔረሰቦች ተገናኝተው ማንነታቸውን የሚያሳውቁበት፣ ባህላዊ እሴቶቻቸውን አጉልተው የሚያሳዩበት፣ ህገመንግሥታዊ መብታቸው መከበሩን የሚገልጹበትና በዚህ ታሪካዊ ቀን ጠንካራ ተሞክሮዎቻቸውን በማጐልበት በተለይም የብሔሮች ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ግንኙነትና አንድነት በማጠናከር አብሮ የመኖር ባህላቸውን እንዲያሣድጉ በማድረግ ረገድ በዓሉ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሃገራችን ህዳሴ አንዱ ገጽታ ነው፡፡ በዓሉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት የሃገሪቱ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተሣስረው የሃገሪቱን ችግር መፍታት እንደሚችሉ በማረጋገጥ በህብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያሳዩበት ታላቅ ፋይዳ ያለው በዓል እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት ፋይዳ የሌለው ስብስብና የበዓል ዝግጅት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ቀደም ብዬ የምመለሰብት እንደሆነ ወደ ጠቆምኩት የዘንድሮው የብሔረሰቦች ቀን መሪ ቃልና እንደምታ ስመለስ  መጀመሪያ መሪ ቃሉን በማስታወስ ይሆናል፡፡ "ህገመንግሥታችን ለብዙህነታችን፣ ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን" ይላል የዘንድሮው 6ኛው የብሔረሠቦች ቀን በዓል መሪ ቃል፡፡

የብሔር ጥያቄን መሰረት ያደረገውና ለጥያቄውም ምላሽ የሰጠው ፌዴራላዊ ስርዓት የብሄሮች ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ድረስ የሚፈቅድና ለዚሁም ህገመንግስታዊ ዋስትና የሰጠ እንደሆነ ይታወቃል።ይህ ዋስትና ደግሞ የዴሞክራሲያችን መለያ ባህርያት ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። የዚህ ህገመንግስታዊ ዋስትና የተሰጠው መብት ሌላው መነሻ ብዙሀነታችን ነው። ስለሆነም ይህ መብት ህገመንግስታዊ ዋስትና የተሰጠው በዋናነት የህዝቦችን ወንድማማችነት በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት ለመፍጠር የሚያስችል የተሻለ አማራጭ ሆኖ በመገኘቱ ነው። እዚህ ላይ አንድነቱ በጋራ አላማና በጋራ እሴቶች ላይ የተመሰረተ እንጂ ሰፊ ግዛት በመያዝ አስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ሊጤን ይገባዋል።

የህዝቦችን የጋራ አላማ በተመለከተ በህገመንግስቱ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚያስችል አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብና በሕዝቦች እኩልነትና አንድነት ላይ የተመሰረተ አንድ የጋራ አገር መገንባት አንደኛውና መሰረታዊው ዓላማ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ አላማቸውንና ራዕያቸውን ለማሳካት ሲወስኑ ብዙህነታቸውን ማስተናገድ የሚችለውንና የቃል ኪዳናቸው መገለጫ የሆነውን ህገ መንግስት በመቀበል ነው።

ህገመንግስቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሄሮችና ብሄረሰቦች እኩልነት ተከብሮ መቀጠል እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል። የእኩልነት መብት ደግሞ የፖለቲካ መብት መሆኑ እሙን ነው። በሌላ አነጋገር አንድ ብሔር/ብሔረሰብ ከሌላው ብሔር ብሔረሰብ ጋር እኩል የሆነ መብት እንዳለው የሚያመለክት ፖለቲካዊ መብት ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዳሴ በዋናነት ህገመንግስታዊ ዋስትና ከተሰጠው የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ያለነዚህ መብቶችም መረጋገጥ የማይቻል እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

እነዚህ የእኩልነት መብቶች በተለይ ከቋንቋ ባህልና ታሪክ አኳያ አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት የሚያሰናክሉ እንጂ የሚያሳኩ እንዳልሆኑ ህገመንግስቱ ከፀደቀበት እለት ጀምሮ የሚናገሩ ሰዎች ቢኖሩም፤ በሂደት የታየው ግን ዓላማውን እንደሚያሳካ ሲሆን ለዚህም ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ እንደአብነት ማንሳት ይቻላል ።

ኢትዮጵያ ብዙህነቷን የሚያስተናግድ የፌዴራል ስርዓት የመገንባቷ ትሩፋት አንድነቷን ማስጠበቅ በመቻሏ ብቻ  የሚወሰን አይደለም። አንዳንድ ከኢትዮጵያ ጋር በሁለንተናዊ መልኩ ተመሳሳይነት ያላቸው ሃገሮች የኛን ሃገር ተሞክሮ መውሰድ ባለመቻላቸው ወይም ባለመፈለጋቸውና የተሳሳተ ፖሊሲ በመከተላቸው ሳቢያ የመበታተን አደጋ እየተጋረጠባቸው እንደሆነ ይኸው እያየን ነው። የኢትዮጵያ መንግስት የአገሪቱን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማይገሰስ መብት የሚያረጋግጥ ስርዓት በአገሪቱ እንዲኖር በማድረጉ ሰላምና መረጋጋት ማስፈን ብቻም ሳይሆን ተከታታይ ዕድገት ማስመዝገብ እንደቻለ በርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶችና የፖለቲካ ተመራማሪዎች

አረጋግጠዋል። በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ ይህንን ብዙሀነቷን የሚያስተናግድና ህገ መንግስታዊ መሰረት ያለውን ፌዴራላዊ ስርዓት ተከታታይነት ባለው ዕድገት ብቻ ሳይሆን ስርነቀል ለሆነ ለውጥ ወይም ህዳሴ መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን በማመን ጉዞውን ተያይዛዋለች።

የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ግምትና ቦታ የሚሰጠው ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በርካታ ብሔር ብሔራሰቦች መብታቸው ተከብሮ ባህላቸውንና ታሪካቸውን ጠብቀው በማጎልበት በቋንቋቸው እንዲማሩና እንዲዳኙ፣ በማንነታቸው የበታችነት ስሜት ሳያድርባቸው እኩልነታቸው በህገመንግስቱ እንዲረጋገጥላቸው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ መሆኑ የመጀመሪያውና መሰረታዊው ምክንያት ቢሆንም ከዚሁ ጋር ተያይዘው በተገኙ በርካታ ውጤቶችም ነው ዕለቱ የተለየ ግምት የሚሰጠው። ከዚህም በተጨማሪ የበለጸገችና በህዝቦቿ መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን እውን በማድረግ ለተከታታይ ዓመታት የተመዘገበውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑም ሌላው ትልቅ ግምት የሚያሰጠው ነው። ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት ሊገኝ የቻለው ከዳር እስከ ዳር የአገሪቱን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ያሳተፈ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እውን እየሆነ መምጣቱና የህዳሴያችንም መሰረት እየሆነ መቀጠሉ ሌላው ተጨማሪ ምክንያት ነው። ይኸው ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገው በልዩነት ውስጥ ያለው አንድነት የህዳሴያችን መሰረት ከመሆን ባሻገር የጉዞው አቀጣጣይ እንደሆነም በህዳሴው ግድብ ተረጋግጧል።

የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት በህገ መንግስቱ መረጋገጡና ዕለቱ በይፋ እንዲከበር መደረጉ ኢትዮጵያዊነት ጎልቶ እንዲወጣ ከማስቻሉም በላይ ዜጎች በፍቅር፣ በመቻቻልና በመከባበር በጋራ እንዲኖሩ ዋስትና የሰጠ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ግን አሁን ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ስንመለከተው የአምስት አመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካትና የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማፋጠን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ላይ የተመሰረተ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ርብርብ ወሳኝ ነው።

ስለሆነም 6ኛውና የዘንድሮው የብሔረሰቦች ቀን "ህገ መንግስታችን ለብዙሀነታችን ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ቃል መከበሩ ተገቢና ወቅታዊ ነው።